# SOLA FIDE

# FAITH ALONE

# በእምነት ብቻ

አዘጋጅ ፡- ተካልኝ ኃ/ሚካኤል

Justification by faith alone is the article on which the Church stands or falls. Thus, "faith alone" is foundational to Lutheranism and Reformed Christianity, and as a formula distinguishes it from other Christian denominations. Martin Luther,

ማርቲን ሉተር በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በድንገት አንድ መግለጫ እንዳየ ይነግረናል። ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ አንብቦ ነበር ነገር ግን በትክክለኛው መንገድ አስተውሎት አያውቅም ። ያየውም ይህ ነው ።

“በወንጌል የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጦአልና፤ ጽድቁም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በእምነት የሆነ ነው፣ “ጻድቅ በእምነት ይኖራል” ተብሎ እንደ ተጻፈው።” ሮሜ 1፥17 ። ያየውም ይህ ነው ። ሉተር ይህን የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል ሲያነብ ቆም ብሎ "ይህ ማለት ምን ማለት ነው? በእምነት የሆነ ጽድቅ አለ? ከእምነት ወደ እምነት ማለት ምን ማለት ነው? ጻድቅ በእምነት ይኖራል ማለት ምን ማለት ነው?" በእዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለ ለሉተር የእግዚአብሔር ብርሃን በራለት ። እናም ጳውሎስ እዚህ ላይ እየተናገረ ያለው እግዚአብሔር በጸጋው ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ለሚቀበሉት ያቀረበው ፅድቅ መሆኑን ይረዳ ጀመር ።

አሰቀድሞ ሰለ መጽደቅ ያለው ምልከታ በሙሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ፣ ፍፁም ውሸት መሆናቸውን በድንገት አየ ። እናም ይህን ባየ ጊዜ የነፍሱን ታላቅ ነጻ መውጣት አገኘ ። ይህንን እውነት መሰበክ ጀመረ እናም ታላቅ የሆነው ተሃድሶ ሆነ ። የሉተር ችግር የኢዮብ ጉዳይ ነበር፦ 'ሰው እንዴት በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ይሆናል?' ( ኢዮብ 9:2 ) ሰው እንዴት በእግዚአብሔር ፊት ሊቆም ይችላል? የሉተርን አምሮና ልብ ያሰጨነቀው ያ ነበር።

ይህም በሰራቸው ያገኙትን ሳይሆን በእምነት የሚያገኙትን ፅድቅ ነው። “ይህ ማለትህ ጳውሎስ የሚናገረው እግዚአብሔር ራሱ ጻድቅ የሆነበት ጽድቅ ሳይሆን እግዚአብሔር በጸጋው በራሱ ጽድቅ ለሌላቸው ሰዎች በነጻ የሚሰጥ ጽድቅ ነው” ብሏል። ስለዚህም ሉተር፦ “**ወዮ እኔ የምድንበት ጽድቅ የእኔ አይደለምን?**” አለ። **ከእኔ ውጭ የሆነ ፅድቅ ነው።** ይኸውም የክርስቶስ ጽድቅ ነው። ሉተርም "ይህን ባወቅሁ ጊዜ ከመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ ተወልጃለሁ የገነትም በሮች ተከፍተው ሄድኩኝ" አለ።

## የሮም ካቶሊክ ሰለፅድቅ ምን ታሰብ ነበር?

የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን መፅደቅ ከመቀደስ በኃላ የሚመጣው ነው ትላለች ። እምነት እና ሌሎች ኃይማኖታዊ ስርአቶችን በመፈፀም በእግዚአብሔር ፊት መቆም እና ቆሞ መቀጠል እንችላለን ትላለች ። የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን እምነት ለመፅደቅ መሰፈርት ቢሆንም ብቻውን ግን በቂ እና የመጨረሻ መሰፈርት አይደለም ብላ ታስተምራለች ። እንደ ምሳሌ አድርገው የሚያቀርቡት፦ oxygen ለመኖር አሰፈላጊ (necessary condition) ነው ። ነገርግን በቂ (sufficient condition). አይደለም ትላለች ። እምነት ብቻውን ለመፅደቅ አሰፈላጊ ካልሆ ተጨማሪ መሰፈርቶችን መፈፀም ያሰፈልገናል ፣ ያለእነዛ ተጨማሪ መሰፈርቶች ህይወት አናገኝም ብላ ታሰተምራለች ።

በተቃራኒው ደግሞ ተኃድሷዊያኑ መቀደስ ከመፅደቅ በኃላ የሚመጣው ነው ። እንዲሁም ያለተጨማሪ መሰፈርቶች ፅድቅን በዕምነት ብቻ እንበቀበላለን ብለው አሰተማሩ ። እግዚአብሔር ፊት ለመቆም እና ቆሞ ለመቀጠል የክርሰቶስ ሰራ ላይ በመደገፍ በማመናችን ብቻ እንፀድቃለን ፣ ጸድወንም እንቀጥላለን ብለው አሰተማሩ ።

## ፅድቅ ምንድነው ?

Justification እና Rightness ትንሽ ለየት ያለ ትኩረት አላቸው።

Justification "ጽድቅን መቁጠር" ወይም " ጻድቅ መባል " የሚታወቅ ህጋዊ አዋጅ ነው። በጳውሎስ መልእክቶች የጽድቅ ትኩረት ባብዛኛው ጥፋተኝነትን በሕግ መልቀቅ ላይ ነው ።

Rightness ግን በአብዛኛው የሚያገለግለው virtuous character በጎነትን ወይን በጎ ስነምግባርን ለማመልከት ነው።

ፅድቅ ማለት ፍፁም የሆነ የሞራል እና የተግባር ንፅህና ነው ። ስለ ፅድቅ ሰናስብ በፍጥነት አእምሮአችን ላይ የሚመጣው እግዚአብሔር ነው ። - ፅድቅ የእግዚአብሔር ባህሪ ነው ፣ ፅድቅ የእግዚአብሔር ገቢር ነው ።

# ሰዎች ይህ ባህሪ እና ገቢር አላቸው ?

ሰዎች ይህ አይነቱ ባህሪ ሆነ ገቢር የላቸውም ። ምክንያቱም ሰዎች ኃጢአተኞች ስለሆኑ ። የሰው ዘር በሙሉ በኃጢአት ስለተበከለ በእግዚአብሔር ፊት ፃድቅ ሊባሉ አይችልም ። ኃጢአት እና ኃጢአተኛ በጨለማ ይመሰላል ። እግዚአብሔር ደግሞ ብርሃን ነው ። ዮሐንስ ደግሞ ብርሃን ከጨለማ ጋር ህብረት እንደሌለው ይነግረናል ። "ከእርሱ የሰማነው ለእናንተም የምንነግራችሁ መልእክት፣ እግዚአብሔር ብርሃን ነው፤ ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም፤ የሚል ነው።" — 1ኛ ዮሐንስ 1፥5 (አዲሱ መ.ት)። ታድያ በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር የተለየ ምስኪን ሰው እንዴት ነው ወደ እግዚአብሔር የሚቀርበው ?

ይህን ጥያቄ እዮብ ይጠይቃል ። "" ነገር ግን ሥጋ ለባሽ በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ጻድቅ ሊሆን ይችላል?" — ኢዮብ 9፥2 (አዲሱ መ.ት) ። የዚህን ጥያቄ ክብደት እንመልከት ።

1ኛ, እንደሚታወቀው ኢዮብ ከክፋት የራቀ ፣ ቅን ፣ እግዚአብሔርን የሚፈራ እርሱን ላለመበደል የሚጠነቀቅ ሰው ነው ። ይህ ሰው ስጋ ለባሽ በእግዚአብሔር ፊት እንዴት መቆም ይችላል ማለቱ በእግዚአብሔር ፊት መቆም እጅግ አሳሳቢ እና ፍፁም የሆነ ንፅህናን የሚጠይቅ መሆኑን እንድንረዳ የሚጋብዝ ነው ።

2ኛ, የኢዮብ መፅሐፍ ከዘፍጥረት መፅሐፍ ቀድሞ የተፃፈ የመጀመሪያ መፅሐፍ ነው ። ይህ ምንን ያሳየናል - የመጀመሪያዎቹ ሰዎች እንኳን ትኩረታቸው ሰው እንዴት በፃድቁ እግዚአብሔር ፊት መቅረብ ፣ መቆም ይችላል የሚል ነው ።

# ፅድቅ ይህን ያህል ለምን አስፈላጊ ሆነ ?

– "ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፤ ይጠግባሉና።" — ማቴዎስ 5፥6 (አዲሱ መ.ት) ። ይህ ከተፈጥሮ ስርአት ጋር የተያያዘ ነው ። ምግብ ለሰዎ ልጆች ህይወት አስፈላጊ እንደሆነ እና የሰው ልጅ ህይወት ቀጣይነቱ በምግብ ላይ እንደሚመሰረት ሁሉ ፅድቅም ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖረን ህብረት እና ለሚኖረን ቀጣይነት መሰረታዊ ነገር ነው ።

– "ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን እሹ፤ እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላችኋል።" — ማቴዎስ 6፥33 (አዲሱ መ.ት) ። በዚህ ክፍል ላይ ሌሎች በረከቶችን ማግኘት የምንችልበትን የበረከት ምንጭ አድርጎ ነው ያቀረበልን ። አንድ ነገር በመፈለግ ሁሉን ነገር ማግኘት ። ይህም የሚያሳየን የሁሉ ነገሮች መሰረት ፅድቅ እንደሆነ ነው ።

**– ፅድቅ ይህን ያህል አስፈላጊ ከሆነ - ሰዎችም በፃድቁ እግዚአብሔር ፊት መቆም የማይችሉ ከሆነ - መፍትሄው ምን ሊሆን ይችላል ?**

ይህንን መፍትሄ ለማወቅ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግኑኝነት ማወቅ ይቀድማል ። እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ያለውን ግኑኝነት መሰረቱ ቃል ኪዳን ነው ። ስለዚህ ቃልኪዳንን መረዳት መሰረታዊ ጉዳይ ነው ።

# ቃልኪዳን

ቃልኪዳን ፦ ሊለወጥ የማይችል ከመለኮት የተሰጠ ህጋዊ ስምምነት ነው ። እግዚአብሔር ከሰው ጋር የሚገናኘው በቃልኪዳን መንገድ ነው ።

– በቃልኪዳን ውስጥ የቃልኪዳን ሰጪው ፣ የቃልኪዳኑ ተቀባይ ፣ የቃልኪዳኑ ተስፋ እና ምልክቱ ፣ እንዲሁም ቃልኪዳኑ የሚፀናበት ከሰው የሚፈለገው መታዘዝ አለ ።

በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ኪዳናት በሶስት መግለጽ እንችላለን ።

## 1ኛ, የቤዛነት ቃልኪዳን

በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር ምክር በተደጋጋሚ ተገልጿል ኤፌ 1:11 ። የቤዛነት ቃልኪዳን የቅዱስ ስላሴ ተሳትፎ ነው ። ይህ አለም ከመፈጠሩ በፉት ያለውን ሁኔታ የሚያሳይ ነው ። ዮሐ 6:38-39 ዮሐ 17:4 ኤፌ 1:4

**– በቤዛነት ቃልኪዳን ውስጥ የአብ ተሳትፎ**

–ህዝቡን የሚመርጥ ፣ ስልጣን ሁሉ በሰማይ እና በምድር የሚሰጥ ፣ በተሰፋው ቃል መሰረት በህዝቡ ላይ መንፈስ ቅዱስን ለማፍሰስ ቃሉን እንደሚፈፅም ። ወዘተረፈ …….

**– የወልድ ተሳትፎ**

* ሰው ሆኖ በሙሴ ቃልኪዳን መሰረት ለመኖር ገላ 4:4 ዕብ 2:14-18 ፣ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ህዝብ መጠበቅ ( እንዳይጠፋ ማድረግ ) ዮሐ 6:39 ።

**– የመንፈስ ቅዱስ ተሳትፎ**

ህዝቡን መቀደስ ፣ ስለ አዳኙ ክርስቶስ መመስከር ፣ ወደእውነት ሁሉ መምራት ። 1ኛ, ጴጥ 1:2 -የሐ 16:13 ።

## 2ኛ, የስራ ቃልኪዳን

ይህ የስራ ቃልኪዳን በእግዚአብሔር እና የሰዎች ሁሉ ራስ ወይንም መካከለኛ በሆነው አዳም መካከል የተደረገ ስምምነት ነው ። በዘፍጥረት ምዕራፍ 1-3 ቃልኪዳን ተብሎ ባይጠራም በቃልኪዳን ሊኖሩ የሚገባቸው ነገሮች ሁሉ በመኖራቸው ቃልኪዳን ማለት እንችላለን ። ነገርግን በሆሴ መፅሀፍ 6:7 በግልጽ በዘፍጥረት 1-3 ያለውን ሁኔታ ኪዳን ብሎ ይጠራዋል ። “እንደ አዳም ቃል ኪዳንን ተላለፉ፤ በዚያም ለእኔ ታማኝ አልነበሩም።” — ሆሴዕ 6፥7 (አዲሱ መ.ት)።

እንዲሁም ዘፍጥረት መፅሐፍ እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ያለው ግነኙነት በቃልኪዳን መሆነኑን መገንዘብ እንችላለን ። ምዕራፍ 1 የእግዚአብሔርን ምጡቅነት የሚያሳይ ነው ። ሙሉውን ምዕራፍ ኤሎሂም ብሎ ነው የሚጠራው ። ኤሎሂም የሚለው ቃል በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከ2,300 ጊዜ በላይ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ኃይሉን እና ሉዓላዊነቱን አጽንዖት ይሰጣል። ኤሎሂም ኃይልን የያዘ፣ የሁሉ ነገር የመጀመሪያ ምክንያት ወይም ፈጣሪ መሆኑን ያመለክታል ።

በምዕራፍ 2 ያህዌ ኤሎሂም ብሎ ነው የሚጠራው ። በዚህ ምዕራፍ የእግዚአብሔርን የቃልኪዳን ስም ነው የሚጠራው ። ያህዌ የሚለው ቃል ደግሞ ከ5,300 ጊዜ በላይ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ዘላለማዊ ህልውናውን እና ህዝቡን ለመርዳት ቁርጠኛ መሆኑ ላይ አጽንዖት ይሰጣል ። ርሁሩህ ፣ የገባውን ቃል የማይረሳ እና ከነናችን ለመሆን ፈቃደኛ የሆነ ማለት ነው ። ከእዚህ የስም አጠቃቀሙ በመነሳት አዳም እና እግዚአብሔር የቃልኪዳን ግኑኝነት እንዳላቸው መረዳት እንችላለን ።

–በዚህ በዘፍጥረት አውድ እግዚአብሔር የቃልኪዳኑ ሰጪ ፣ አዳም የቃልኪዳኑ ተቀባይ ነው ።

– የቃልኪዳኑ ተሰፋ ፦ የዘላለምን ህይወት ተሰፋ በገነት እግዚአብሔር ለሰው ሰጠ። ሰው ሲፈጠር ህይወት

ነበረው ። ሞት አልነበረም ። በዚህ ሁኔታ ቢኖር ለዘለአለም እንደሚኖረው ተሰፋ ነበረው ።

– የቃልኪዳኑ ምልክት ፦ የህይወት ዛፉ ነው ።

– ቃልኪዳኑ የሚፀናው በሰዎች መታዘዝ ነው ። 2:9 -3:22

በዚህ ቃልኪዳን ሞት የህይወት ተቃራኒ ነው ።ይህ ሞት ስጋዊ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊም ሞት ጭምር ነው ። ማለትም ከእግዚአብሔር መለየትንም ያካትታል ።

ለአዳም ብቻ ሳይሆን ከአዳም ለሚወለዱ በሙሉ እና አዳም ለወከላቸው ሰዎች በሙሉ ነው ።

ቃልኪዳን በረከት እና እርግማን አለው ። ቃልኪዳኑ የሚሰራው ቃልኪዳኑን ለመቀበል አካል ብቻ ሳይሆን ለዘሩም ጭምር ነው ። በዚህም ምክንያት እነዚያ ሰዎች የቃልኪዳኑ በረከትም ሆነ እርግማን ታካፈይ ይሆናሉ ።

የቃልኪዳኑ ተቀባይ ለቃልኪዳኑ ታማኝ ከሆነ በረከቱ ለእርሱ እና ለዘሮቹ (ለወከላቸው) ይሆናል ። ለቃልኪዳኑ ታማኝ ሆኖ ካልተገኘ ግን እርግማኑ ለእርሱ እና እሱ ለወከላቸው ሁሉ ይሆናል ። ለምሳሌ ይህን እንመልከት ፦ “..፤ በአባቶች ኀጢአት ልጆችን የልጅ ልጆቻቸውን እስከ ሦስትና አራት ትውልድ ይቀጣል።”” — ዘጸአት 34፥7 (አዲሱ መ.ት) ።

እንዲሁም ፦ “ለሚወዱኝና ትእዛዞቴን ለሚጠብቁ ግን እስከ ሺህ ትውልድ ቸርነትንና ፍቅርን እገልጣለሁ።” — ዘዳግም 5፥10 (አዲሱ መ.ት)

ይህ የቃልኪዳን ሰርአት ነው ። ይህ ደግሞ በአዳምም የተገለጠ ነው ። ወድቀቱ ለአዳም ብቻ ሳይሆን ከአዳም ለሚወለዱ በሙሉ እና አዳም ለወከላቸው ሰዎች በሙሉ ነው ።“በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኀጢአተኞች እንደሆኑ፣ ....” — ሮሜ 5፥19 (አዲሱ መ.ት)።

ይህ ወክልና መፅሐፍ ቅዱስ ላይ በሰፊው ተገልጿል ። ለምሳሌ የዳዊት እና የጎልያድን የውክልና ተግባር መመልከት እንችላለን ። “ከእኔ ጋር ሊዋጋና ሊገድለኝ ከቻለ፣ እኛ ባሪያዎቻችሁ እንሆናለን፤ እኔ ባሸንፈውና ብገድለው ግን እናንተ ባሪያዎቻችን ትሆናላችሁ፤ ትገዙልናላችሁ።”” — 1ኛ ሳሙኤል 17፥9 (አዲሱ መ.ት)

ህዝቡን የሚወክሉ ሁለቱ ተፋላሚዎች ናቸው ። በዚህ ፍልሚያ ዳዊት የሚያሸንፍ ከሆነ የፍልስጤም ህዝብ በሙሉ ለእስራኤልያዊያን ባርያ ይሆናሉ ። እንዲሁም ጎልያድ የሚያሸንፍ ከሆነ የእስራኤል ህዝብ በሙሉ ለፍልስጤማውያን ባሪያዎች ይሆናሉ ። በዚህ ውጊያ ሙሉ የእስራኤል ህዝብ እና ሙሉ ፍልስጤም አልተዋጉም ። በወከላቸው አካል በኩል የድሉም የውርደቱም ተካፋይ ይሆናሉ ።

እንዲሁም ፦ ይህንን አይነት አገላለጽ በዕብራውያን መልዕክት በሙግት መልክ በግልጽ ተቀምጦ እናያለን ። ዕብራውያን 7 (አዲሱ መ.ት)[8] በአንድ በኩል ዓሥራት የሚቀበሉት ሟች ሰዎች ናቸው፤ በሌላ በኩል ግን ሕያው ሆኖ እንደሚኖር የተመሰከረለት ይቀበላል። [9] እንዲያውም ዓሥራት የሚቀበለው ሌዊ፣ ራሱ በአብርሃም በኩል ዓሥራት ከፍሎአል ማለት ይቻላል፤ [10] ምክንያቱም መልከጼዴቅ አብርሃምን ባገኘው ጊዜ፣ ሌዊ ገና በአባቱ በአብርሃም አብራክ ነበር። ሌዊ ገና ሳይወለድ በአብረሃ ወገብ እያለ አብረሃም ለመልከፄዴቅ አሰረት በመክፈሉ ሌዊም አብሮ ከፍሏል እያለን ነው ። በእነዚህ መረጃዎች መሰረት በማድረግ አዳም ህዝቡን በሙሉ እንደወከለ እና ህዝቡ በሙሉ የኃጢአቱ እና የቅጣቱ ተካፋይ መሆኑን መገንዘብ እንችላለን ። Original Sin በዚህ በግልጽ ይታያል ።

## 3ኛ, የፀጋ ቃልኪዳን

ሰው ከስራ ቃልኪዳን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ከወጣ በኃላ እግዚአብሔር ለሰዎች ልዩ ቃልኪዳን ገባ። ይህም ቃልኪዳን በቤዛነት ቃልኪዳን የሚመሰረት የፀጋ ቃልኪዳን ነው ።

የፀጋ ቃልኪዳን ሁኔታ

1 የፀጋ ቃልኪዳን ሰጪው እግዚአብሔር ነው ። ቃልኪዳን ሲሰጥ ከሰው ጋር አልተማከረም ። በመሰረቱ ይህንን ቃልኪዳን መግባት ግዴታው አልነበረም ። ነገርግን ከፀጋው ለሰዎች በነፃ ሰጠ ።

2, የፀጋ ቃልኪዳን ተቀባይ የእግዚአብሔር ህዝብ ነው ። ክርስቶስ የህዝቡ ራስ እና ዋስ ነው ። ሮሜ 5:18-19 - 1ኛ ቆሮ 15:22 ኤፌ 1:22 ፣ ክርስቶስ ኪዳኑን ለሚቀበሉት የሚፈለግባቸውን ለመፈፀም የዚህ ቃልኪዳን መካከለኛ ነው ዕብ 8:6 - 9:15 - 12:24 ።

3 የፀጋው ቃልኪዳን ተካፋይ ለመሆን የሰው እፀፋ ያስፈልጋል ። ይህም ዕምነት ነው ። መታዘዝ በቃልኪዳን ውሰጥ ሰው ለመኖሩ ምልክት እና ማረጋገጫ ነው ። ኤፌሶን 2:8-10 1ኛ ዮሐ 2:4-6 ። የኪዳኑ ምልክት ጥምቀት እና የጌታ እራት ነው ። 1ኛ ቆሮ 11:23-26 ። 4, የፀጋው ቃልኪዳን ተሰፋ የዘለአለም ህይወት ነው ። ዮሐ 3:16 _ 36 ሮሜ 6:23 1ኛ ጴጥ 3:5

**– ማንኛውንም ቃልኪዳን ውል እና ስምምነት አለው ።**

1 የቃልኪዳኑ ውል እና ስምምነት

2 በቃልኪዳን ውስጥ የህይወት አኗኗር ።

ይህ የፀጋ ቃልኪዳን መካከለኛ በሆነው ኢየሱስ ፍፁም ታዛዥነት ምክንያት ፀንቷል ፣ አማኞች በእምነት ብቻ ከክርስቶስ ጋር አንድ አካል ሆነው ይኖራሉ ። ክርስቶስ የህዝቡ እውነተኛ እና ፍፁም ወኪል ነው (federal or covenantal head)። የፀጋው ቃልኪዳንም ብቸኛ መካከለኛ ሆኖ በመገኘት በህዝቡ ምትክ እግዚአብሔር ከመልኩ ተሸካሚዎች የሚፈልገውን ፍፁም መታዘዝ ለእግዚአብሔር ህግ ታዟል ። እንዲሁም በአዳም በመወከላቸው እና አዳም ባለመታዘዙ እንዲሁም በአዳም እና በወከላቸው ሰዎች ሊመጣባቸው የሚገባውን የእግዚአብሔር ቁጣ እና ፍርድ በራሱ ላይ በማድረግ ፍፁም ምትካዊ መሰዋዕት(substitutionary atonement) በመሆን ሞቶላቸዋል ። በዘመን ፍፃሜ ሊሆን ያለውን የእግዚአብሔር ፍርድ ክርስቶስ በዘመን መሀል በመምጣት እና የእግዚአብሔርን ቁጣ በመቀበሉ ከሚመጣው የእግዚአብሔር ቁጣ ህዝቡን ነፃ አውጥቷል ። የነሱን ኃጥያት በክርስቶስ(imputation of our sin in christ) እንዲሁም የክርስቶስን የፅድቅ ስራ ደግሞ ለነሱ በመቁጠር (imputation of Christ's righteousness both in his active and passive obedience)። ወይንም አባቶች እንደሚሉት Alien righteousness አስቆጠረላቸው ።

ከዛም ከሞት በመነሳት እግዚአብሔር አስቀድሞ በስራ ቃል ኪዳን ለአዳም ፍፁም ቢታዘዝ ኖሮ ይሰጠው ዘንድ ተሰፋ ወደሰጠው ብክለት ወደሌለበት የአዲስ ፍጥረት ሁኔታ እና ክብር አስገብቷቸዋል ። እንዲሁም የማያቋርጥ ሊቀ ካህናዊ ስራ በመስራት ወደራሱ ፍፃሜ እና እርስት እንድንገባ ክርስቶስ በቂ እና ሌላ ሊጨመርበት የማይፈልግ ፍፁም ስራ ብቻ በእግዚአብሔር ዘንድ ለዘለዓለም እንቆማለን ።

– የፅድቅ ምንጭ የእግዚአብሔር ፀጋ ነው ። ሮሜ 3:25-26

– የፅድቅ መገኛ የክርስቶስ መታዘዝ ነው ። ሮሜ 5:18-19

– የፅድቅ መንገድ እምነት ነው ።ሮሜ 3:28 - 5:1-2።

– በዚህ የፀጋ ቃልኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ከሰው ጋር አልተማከረም ፣ ክርስቶስ የቃልኪዳኑ ራስ እና ተወካይ በመሆኑ ለቃዳኑ ታማኝ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ታዛዥነቱን ፈፅሟል ። የቃልኪዳኑ ተቀባይ የሆኑት ህዝቡ ደግሞ የክርስቶስ ኢየሱስን ስራ ለመቀበል የሚጠበቅባቸው ወይንም የክርስቶስ ኢየሱስ ፅድቅ እንዲቆጠርላቸው እና በእግዚአብሔር ፊት መቆም እንዲችሉ እምነት ያስፈልጋቸዋል ። በክርስቶስ ኢየሱስ የተሰራው ስራ ሙሉ እና ፍፁም በመሆኑ ሌሎች ተጨማሪ ስራዎች አላስፈላጊ ይሆናሉ ። እምነት ብቻውን የክርስቶስን ፅድቅ እንድንቀበል ያደርገናል ።

j.i. packer. Faith is "an appropriating instrument, an empty hand outstretched to receive the free gift of God's righteousness in Christ." ጄ አይ ፓከር እንደዚህ ይላሉ ፦እምነት “የእግዚአብሔርን የጽድቅ ስጦታ በክርስቶስ ለመቀበል የተዘረጋ ባዶ እጅ” ነው።

የፀጋን ቃል ኪዳንም ፀጋ ያሰኘው ለሰዎ ልጆች በነፃ የተሰጠ የእግዚአብሔር ስጦታ ስለሆነ ነው ። ፀጋ ፀጋ እንዲሆን የሰው እጅ መግባት የለበትም ። ፀጋ በሰዉ ልፋትና የጽድቅ ስራ የሚገኝ ሳይሆን– እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የሰራዉን የተጠናቀቀ የደህንነት ስራ ነው ። እጅግ ንፁህና ቅዱስ የሆነዉ አምላክ

እጅግ በጣም ኃጢያተኛ ከሆነዉ ሰዉ ጋር የሚገናኘዉና ህብረት የሚያደርገዉ በፀጋዉ አማካኝነት ብቻ ነዉ!! ፀጋ በዓለም ከሚፈፀመዉ ኃጢያት በሙሉ ከመጠን ይልቅ እጅግ የሚበልጥና በእምነት ለሚቀበሉት ሁሉ ደኅንነትን (የዘላለምን ህይወት) የሚያስጥ የእግዚአብሔር የማዳን አሰራር ነዉ!!

## – በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህንን አይነት አገላለጽ በሰፋት ተዘግቦ እናገኛለን ። ለዚህ ሀሳብ በዋናነት የሮሜን መፅሐፍ ምዕራፍ 4 ፡ 1-8 ላይ መሰረት በማድረግ ለመመልከት እንሞክር ።

ሮሜ 4 (አዲሱ መ.ት) [1] እንግዲህ በሥጋ የቀድሞ አባታችን የሆነ አብርሃም በዚህ ረገድ ምን አገኘ እንላለን? [2] አብርሃም በሥራ ጸድቆ ቢሆን ኖሮ፣ የሚመካበት ነበረው፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት መመካት አይችልም። [3] መጽሐፍስ ምን ይላል? "አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።" [4] አንድ ሰው ሥራ ከሠራ ደመወዙ እንደ ስጦታ ሳይሆን እንደ ተገቢ ዋጋው ይቈጠርለታል። [5] ነገር ግን ለማይሠራው፣ ኃጥኡን ሰው ጻድቅ በሚያደርግ በእግዚአብሔር ለሚያምን ሰው፣ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርለታል። [6] ዳዊትም ጽድቅ ያለ ሥራ ስለሚቈጠርለት ሰው ብፅዕና እንዲህ ብሎአል፤ [7] "መተላለፋቸው ይቅር የተባለላቸው፣ ኀጢአታቸው የተሰረየላቸው፣ ብፁዓን ናቸው።[8] ኀጢአቱን፣ ጌታ ከቶ የማይቈጥርበት ሰው ብፁዕ ነው።"

– እስካሁን ባየነ መንገድ ፅድቅ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት እንዴት እቆማለሁ ? ነው ትልቁ ጥያቄ ። በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው በስራ የመፅደቅ እና በዕምነት የመፅደቅ ተቃርኖ በግልጽ እንረዳለን ። ጳውሎስ እኛን ሁላችን በስራ መፅደቅ አንችልም ብሎ ሲል ። አብርሃምንስ ምን ትለዋለህ አይነት ነገር ነው ።

**ቁጥር 1፦** "እንግዲህ በሥጋ የቀድሞ አባታችን የሆነ አብርሃም በዚህ ረገድ ምን አገኘ እንላለን?"

አንዳንድ ተርጓሚዎች እንደሚሉት ክፍሉ በቀጥታ ከተረጎምነው አባታችን አብረሃም በስጋ የሆነ ነው የሚለው ይላሉ። ነገርግን አንዳንዶች እንደሚሉት Jhon Calvinንንም ጨምሮ ጳውሎስ ይህንን ባይጠቀም ኖሮ እንደ ንቀት ይቆጠርበታል ። ስለዚህ አነሱ በሚፈልጉበት መጥቶ argumentን ለማደራጀት ነው ይላሉ ።

**ቁጥር 2፦** "አብርሃም በሥራ ጸድቆ ቢሆን ኖሮ፣ የሚመካበት ነበረው፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት መመካት አይችልም።" ቢሆን ኖሮ if የሚለው ቃል በራሱ አብረሃም በስራ እንዳልፀደቀ የሚያሳይ ነው ። በእግዚአብሔር ፊት የሚለው ደግሞ ነገሩን በጣም ነው የሚያጎላው ። ዳኛው እግዚአብሔር ነው ። በዚህ ፍፁም እና ንፁህ እግዚአብሔር ፊት እንዴት በራሱ ስራ ፃድቅ ነው ሊባል ይችላል ?? ።

አብረሃም በስራ ፀድቆ ከሆነ በእግዚአብሔር ፊት የሚኩራራበት ነገር አለው ። በእግዚአብሔር ፍርድ ፊት ከእግዚአብሔር ክፍያ የምናገኘው የራሳችን ስራ ሲኖረን ብቻ ነው ። ይህም በሞዕ 2:7 የተገለፀ ነው ። የአብርሃም ጉዳይ የአይሁድ ሁሉ ማዕከል ነው ። በቀላሉ የአብርሃም ጉዳይ የአንድን አይሁዳዊ ትኩረት በቀላሉ ይሰባል ። በእነሱ አመለካከት አብረሃም በስራው ነው የፀደቀው ። Leon morris አይሁዳዊያን አብርሃምን በተመለከተ ምን እንደሚያስቡ እንዲህ በማለት ይገልፃል ፦ ከ66ቱ ውጪ ያሉት የአይሁዳውያን ፅሁፎች ላይ እንደሚገልፀው አብረሃም ህግን ሁሉ ፈፅሟል ።

ጳውሎስ አብረሃም በስራ እንዳልፀደቀ ያረጋግጥልናል ። ይህንንም የሚገለፀው በእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም ብሎን ነው ። ጳውሎስ ይህንን ለማስረዳት ከብሉይ ኪዳን መፅሀፍ እየጠቀሰ proof ለመድረግ ይሞክራል ። ዘፍ 15:6 "አብራም እግዚአብሔርን (ያህዌ) አመነ፤ እርሱም ጽድቅ አድርጎ ቈጠረለት።" ጳውሎስ የአብርሃም እምነት ከፊት ለፊት ባለ እውነታላይ እንደሆነ ማስረዳት ነው አላማው ።

**ቁጥር 3** “መጽሐፍስ ምን ይላል? “አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።””

ይህ አባባል ከስራ በተቃራኒ ሆኖ ነው የቀረበው ። አብረሃም በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ ሊያስገኝለት የሚችል ህግ አልጠበቀም ፣ አገልግሎትም ሆነ ሃይማኖታዊ ስርአትም አልፈፀመም ። ፅድቅ በራሳችን የፈጠርነው ነገር አይደለም ። እንዲሁም በእኛ ኃይል ውስጥ ያለም ነገር አይደለም። በሰዎች ውስጥ ከጥፋት በስተቀር ምንም ነገር የለም ። ድነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ ነው ።

ዘፍጥረት 15:6 ላይ አብረሃም ያመነው እግዚአብሔር ልጅ እንደሚሰጠው ነው የሚለው ቀድሞ አእምሮአችን ላይ የሚመጣው ። ነገርግን የምርም እግዚአብሔር ይሰሃቅን ይሰጠኛል የሚለው እምነት የወንጌል እምነት ነው ብሎ ማሰብ ይከብዳል። ልጅ ከመውለድም ከፍ ያለ ትርጉም ነው ። የመዳን ቃልኪዳንን እና የልጅነትን ፀጋ ነው ። እግዚአብሔር በምዕራፍ 12 በዘርህ ምድርን እባርካለሁ ሲል በምዕራፍ 3 ካለው እርግማን በተቃራኒዉ ነው ። በአዳም ምክንያት ምድር ተረግማለች በአብረሃም ዘር ምክንያት ደግሞ በረከት እንደሚመጣ እየተናገረ ነው ።

ጳውሎስ በገላትያ መልዕክቱ ደግሞ ይህንን ሃሳብ አጉልቶ ነው የሚያሳየን ። እግዚአብሔር ለአብርሃም ወንጌልን ሰብኳል ። አብረሃምም ያመነው ይህንን ወንጌል ነው ይለናል ። ገላትያ 3 [6] እስቲ አብርሃምን አስቡ፤ “እርሱ እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።” [7] እንግዲህ እነዚያ የሚያምኑት የአብርሃም ልጆች እንደሆኑ አስተውሉ። [8] መጽሐፍ፣ እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንደሚያጸድቅ አስቀድሞ በማየት፣ “አሕዛብ ሁሉ በአንተ ይባረካሉ” በማለት ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ አስታወቀው።

John Calvin እንደዚህ ይላል ። “ በዘርህ የሚለው ለእነርሱ ቀላል ትርጉም የለውም ። አብረሃም በክርስቶስ ውስጥ ያለውን ማዳን እያሰበ ነው ”ይላል። በዚህ ክፍል የምንረዳ ፦ ጥያቄው በእግዚአብሔር ፊት እንዴት እንቅረብ ወይንም እንዴት ከእግዚአብሔር ቁጣ እንዳን እንጂ ህይወታችንን እንዴት እናስተዳድር እያለ አይለም።

**ቁጥር 4 - 5፦** “እንድ ሰው ሥራ ከሠራ ደመወዙ እንደ ስጦታ ሳይሆን እንደ ተገቢ ዋጋው ይቈጠርለታል።”“ነገር ግን ለማይሠራው፣ ኃጥኡን ሰው ጻድቅ በሚያደርግ በእግዚአብሔር ለሚያምን ሰው፣ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርለታል።”

– ደሞዝ ስጦታ አይደለም።

– ስጦታም ደሞዝ አይደለም ።

ለምሳሌ የመንግስት ስራ የምንሰራ ከሆነ በየቀኑ ለምነሰራውን በእየቀኑ ደሞዝ አይከፈለንም በወሩ መጨረሻ ነው የሚከፈለን ። ስለዚህ ደሞዝ ለሚከፍለን መንግስት የየቀኑ ገንዘብ እዳ ሆኖ ይቀመጥበታል ። ደሞዛችንን ስንቀበል የልፋታችን ነው የምናገኘው በሚል መንፈስ እንጂ በአይገባኝም በሚል ስሜት አይደለም ። ስለዚህ እዳ እንደ ሚቀበል ሰው እንጂ እንደ ባለእዳ አይደለንም ።

ነገርግን በቁጥር 5 የተገለፀው ሰው ከዚያ በተቃራኒ ነው ።

1ኛ, የማይሰራ ነው ።

2ኛ, በእግዚአብሔር የሚያምን ነው ።

3ኛ, ፅድቅ የተቆጠረለት ሰው ነው ።

ይህ ስጦታ ከመባል ውጪ ምን ሊባል ይችላል ? ስጦታ በሰጪው በጎ ፈቃድ ላይ የሚመሰረት ነው ። ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ የኃጢአት መስዕዋት ከመሆኑ በቀር ምን እናምናለን ?

አንዳንድ አስተማሪዎች እንደሚሉት "የኃጢአትን ይቅርታ እንድናገኝ የእግዚአብሔርን ፅድቅ በሰራ ማርካት አለብን ይላሉ" ። በኃጢአት ይቅርታ ውስጥ ጣልቃ የሚገቡ ስራዎች ካሉ ላለመዳን 100% ወደኋላ አፈግፍገዋል ። መዝሙረኛው ዳዊት ጌታ ኃጢአቱን እንደማይቆጥር አስቀድሞ ተናግሯል ። እግዚአብሔር የማይቆጥራቸውን ኃጢአቶች እንዴት ይቀጣል ? እንዴትስ በሰራቸው ይቅር ለማለት ያስባል ። ይህ አስተሳሰብ ወጥነት የለውም ። አንድ ከው በክርስቶስ ሲያምን ያ እምነቱ ፅድቅ ያስገኝለታል ።

**ቁጥር 5-8 ።** [6] ዳዊትም ጽድቅ ያለ ሥራ ስለሚቈጠርለት ሰው ብፅዕና እንዲህ ብሎአል፤ [7] "መተላለፋቸው ይቅር የተባለላቸው፣ ኀጢአታቸው የተሰረየላቸው፣ ብፁዓን ናቸው። [8] ኀጢአቱን፣ ጌታ ከቶ የማይቈጥርበት ሰው ብፁዕ ነው።"

በዚህ ቁጥር ሰው በሰሪው አይፀድቅም የሚለውን ለማሳየት ፅድቅ ያለ ስራ ስለሚቆጠርለት ሰው ያነሳል ። ይህ ሰው እንዴት ነው ያለሰራው ፅድቅ የሚቆጠርለት ? ኃጢአቱ በመደምሰስ እና ዳግመኛ ኃጢአቱ ላይታወስ እንዲሁም ኃጢአት ሰርቶ እንደማያውቅ በመቁጠር ነው ።

ይህ በቁጥር 17-21 ባለው የተብራራ ነው ። አብረሃምን ለዚህ ምሳሌ አድርጎ ያነሳል ። አብረሃምን ሲገልፀው ፦ በእምነቱ የፀና ፣ ለእግዚአብሔር ክብርን የሰጠ ፣ የእግዚአብሔርን ተስፋ ያልተጠራጠረና በሙሉ ልብ እርግጠኛ የሆነ ። ይህን ታሪክ በቀጥታ ዘፍ 17 የሚያመለክት ነው እንጂ አብረሃም ልጁን በመሰዊያው ላይ ባቀረበ ጊዜ አይደለም ። [17] አብርሃምም በግንባሩ መሬት ላይ ተደፋ፤ ሣቀና በልቡ፣ "እንዲያው ምንስ ቢሆን የመቶ ዓመት ሽማግሌ የልጅ አባት መሆን ይችላልን? ሣራስ በዘጠና ዓመቷ ልጅ መውለድ ትችላለችን?" አለ።

[18] አብርሃም እግዚአብሔርን (ኤሎሂም)፣ "እስማኤልን ብቻ ባርከህ ባኖርህልኝ" አለው ።

በእውነት ግን በዚህ ታራክ ውስጥ አብረሀም አልተጠራጠረም ? በእውነት ግን በእምነቱ ፀንቷል እንዲሁም ለእግዚአብሔር ክብርን ተሰጥቷል ?

በተቃራኒው ነው ። እግዚአብሔር የሰጠውን የተሰፋ ቃል ተጠራጥሯል ። እንደውም አንተ ይስሃቅ የምትለው ይቅርና በእስማኤል ተሰፋህን ፈፅም ብሎታል ። ይህ ብቻ አይደለም ወደ ጋር ገብቷል ።

ታድያ ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 4 ላይ በእምነቱ ፀና አልተጠራጠረም ለምን አለን ?

መልሱ ከላይ የተናገረውን እያብራራው ስለሆነ ።ከቶ የማይቈጥርበት ሰው ብፁዕ ነው።" ሰው ከፀጋ ከሆነ ኃጢአቱ አይቆጠርለትም ይለናል ። አብረሃምም ከፀጋ ስለሆነ እነዚህ ሁሉ ኃጢአቶች አልተቆጠሩለትም ይለናል ። አልተቆጠረም ቢልም ግን ሌላ የተቆጠረ ነገር አለ ። እርሱም ፅድቅ ነው ። ይህ ፅድቅ ደግሞ ለእርሱ ብቻ አይደለም ። ለእኛም ጭምር የሚቆጠር ነው ።

ሮሜ 4 ፡ [23] "ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት" የሚለው ቃል የተጻፈው ለእርሱ ብቻ አይደለም፤ [24] ነገር ግን እግዚአብሔር ጽድቅ አድርጎ ለሚቈጥርልን፣ ጌታችን ኢየሱስን ከሙታን ባስነሣው በእርሱ ለምናምን ለእኛም ጭምር ነው። [25] እርሱ ስለ ኀጢአታችን እንዲሞት ዐልፎ ተሰጠ፤ እኛን ጻድቅ አድርጎ ለማቅረብም ከሞት ተነሣ።

በዚህ ክፍል ደግሞ የአብረሃምን እምነት ከእኛ ጋር ያመሳሰለዋል ። ይህ የዘፍጥረት 22ትን ታሪክ አብረሃም ልጁን ይስሃቅን በመሰዊያ ሲያቀርብ ያለውን ሁኔታ የሚያነሳ ነው ። የዕብራውያን ፀሀፊ እንደሚነግረን፦

“አብርሃም እግዚአብሔር ሙታንን ሊያስነሣ እንደሚችል ተገንዝቦ ነበር፤ ይስሐቅንም ከሞት የመነሣት አምሳያ ሆኖ አገኘው።” ዕብራውያን 11፥19 (አዲሱ መ.ት)

በዚህ ክፍል አብረሃም እግዚአብሔር አብ ሙታንን እንደሚያስነሳ አምኗል ።

እኛም ልክ እንደሱ እግዚአብሔር አብ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን እንዳስነሳው አምነናል ። ስለዚህ ለአብርሃም የተቆጠረው ፅድቅ ለእኛም ይቆጠራል ። ይህ ማለት ኢየሱስ የሞተው የእኛን በደል አስወግዶ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ አድርጎ ለመቅረብ መሆኑን በማመን ላይ ነው ።

አንድ ሰው ክርስቶስን አምናለሁ ስላለ ብቻ አማኝ ነው ማለት አይቻልም ። ስለክርስቶስ ምንድነው የሚያምነው ነው ትልቁ ጥያቄ ?

ጆን ቡንያን በመናኝ ጉዞ ላይ እንደፃፈው .....

በዳንዴ እና በክርስቲያን መካከል የተደረገው ንግግር

ከብዙ ንግግር በኋላ ..

ዳንዴ ፦ በአጭር ቃል ለመፅደቅ በክርስቶስ ኢየሱስ ማመን እንዳለብኝ አውቃለሁ ።

ክርስቲያን ፦ እንዴት? ክርስቶስ እንደሚያስፈልግህ ሳትረዳ በእርሱ ስለማመን እንዴት ታስባለህ? አንተ ዘወትር ስለ ሃጥያትህ አታስብም ። ስለ ራስህ እና ስለምግባርህ ከፍ ያለ አስታየት ስላለህ በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም የእግዚአብሔር ፅድቅ እንደሚያስፈልግህ ከቶ እንዳልተረዳህ ግልፅ ነው ። እንግዲህ እንዴት ነው በክርስቶስ አምናለሁ የምትለው ?

ዳንዴ ፦ የሆነው ሆኖ እንደሚገባኝ አምናለሁ ።

ክርስቲያን ፦ እንዴት ታምናለህ?

ዳንዴ፦ ክርስቶስ ስለ ኃጢአተኞች እንደሞተ አምናለሁ ።

ህጉንም በመታዘዜ በፀጋው ስለሚቀበለኝ ከመርገም ድኜ በእግዚአብሔር ፊት እንደምፀድቅ አምናለሁ ። ክርስቶስ ከቱርፋቱ የተነሳ የአምልኮዬን ስራ በአባቱ ዘንድ የተቀበለ ስለሚያደርገው እፀድቃለሁ ። ( ስራዬን እኔ እስራና የጎደለውን ኢየሱስ ያስተካክልልኛ እና በእግዚአብሔር ፊት ያቀርብልኛል ። በዚህ Ground እድናለሁ ይላል ። ክርስቶስ በዚህ ረገድ ያስፈልገኛል ይላል ።

ክርስቲያን፦ ስለዚህ ሃይማኖትህ መልስ ልስጥህ ።

1ኛ, የያዝከው ሀይማኖት አስደናቂ ሃይማኖት ነው ።

ስለምን ይህ ሃይማኖት በእግዚአብሔር ቃል ተፅፎ አይገኝም ?

2ኛ, በሃስተኛ ሃይማኖት ታምናለህ ። በክርስቶስ በተገኘው ፅድቅ ረገድ የራስህን ፅድቅ ታቆማለህ ።

3ኛ, እንደ ሃይማኖትህ ክርስቶስ የምግባርህ እንጂ የአንተ አፅዳቂ አይደለም ።

በዚህ የምንመለከተው በክርስትና እምነት እና በሌሎች ኃይማኖት መካከል ያለ ልዩነት እንጂ በአንድ ቤተ ዕምነት ውስጥ ያለ የአመለካከት ልዩነት አይደለም ።

## ለምን በዕምነት ብቻ ማለታችን አስፈላጊ ሆነ?

ምክኒያቱም እውነተኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወንጌል ከሐሰት ወንጌሎች የምንለይበት አንዱ መለያ ባህሪ ስለሆነ ! በዕምነት ብቻን መካድ ወይንም በዕምነት ብቻ የሚለውን ትርጉሙን መቀየር አደጋ ላይ ያለው ወንጌል መያዝን የሚያሳይ ነው ።

በእምነት ብቻ በፕሮቴስታንቶች እና በካቶሊኮች መካከል ያለ ልዩነት ብቻ ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱሳዊው ክርስትና እና በሁሉም ሃይማኖቶች እንዲሁም ትምህርቶች መካከል ያለው ልዩነት ቁልፍ ነጥብ ነው።

በእግዚአብሔር ጻድቅ ናችሁ የተባልነው በሥራ ሳይሆን በእምነታችን ብቻ ነው የሚለው ትምህርት የመጽሐፍ ቅዱስ መሰረታዊ ትምህርት እና አብዛኞቹን የአምልኮ ሥርዓቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና የሚለያይ መስመር ነው። አብዛኞቹ ሃይማኖቶች እና የአምልኮ ሥርዓቶች ሰዎች ለመዳን ምን መሥራት እንዳለባቸው ቢያስተምሩም፣ መጽሐፍ ቅዱስ ግን የዳንነው በሥራ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጸጋ በእምነት ስጦታ እንደሆነ ያስተምራል ።

መጽሐፍ ቅዱሳዊው ክርስትና ከየትኛውም ሀይማኖቶች የሚለየው እግዚአብሔር በክርስቶስ የጨረሰው ስራ ባከናወነው ነገር ላይ ያተኮረ ሲሆን- ሁሉም ሌሎች ሃይማኖቶች ግን በሰዎች ስራ ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

በእምነት የመጽደቅን ትምህርትን ከተውን፣ ብቸኛውን የመዳን መንገድ እንተወዋለን። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን የክርስቶስ ፅድቅ እምነት ብቻ እንደሚቆጠርልን ያስተምራል። የእሱ ፅድቅ ለእኛ ይቆጠራል (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21)። የራሳቸውን ፅድቅ ለመመስረት የሚሞክሩ ወይም እምነትን ከስራ ጋር የሚደባለቁ ሁሉ የእግዚአብሔርን ፍፁም የመመዘኛ ደረጃን መውጣት ይጠበቅባቸዋል ። Sola fideን የሚክዱ ሊያድናቸው የሚችለውን ብቸኛ ወንጌል አይቀበሉም እናም በግድ የሐሰት ወንጌልን ይቀበላሉ።

## በህይወት መዝገብ ላይ ሰራችን ሳይሆን ሰማችን ተፅፏል ፣ ሰማችን እንዲፃፍ ሰራችን በክርስቶስ ተሰርቷል !!!!